መልእክት አራት

## ኢዮብ እና ሁለቱ ዛፎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ዘፍ. 2፡9፣ 17፤ ራእ. 22፡1-2፣ 14፤
ኢዮብ 1፡1፤ 2፡3፤ 4፡7-8፤ 42፡1-6፤ ሮሜ 8፡5-6

**I. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው መለኮታዊ መገለጥ መሠረት፣ ሁለት ዛፎች፣ ሁለት ምንጮች፣ ሁለት መንገዶች፣ ሁለት መርሆች እና ሁለት መጠናቀቆች አሉ፡-**

ሀ. የሕይወት ዛፍ የሚያመለክተው ሰው [ከሦስታንዱ አምላክ] ጋር ባለው ግንኙነት ሦስታንዱ አምላክ ለሰው እንደ ሕይወት መሆኑን ነው፤ የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ፊት በነበረው የሰው ውድቀት ሰይጣን፣ ዲያቢሎስ፣ ክፉው ለሰው እንደ ሞት መሆኑን ነው—ዘፍ. 2፡9፣ 17፤ መዝ. 36፡9።

ለ. የሕይወት ዛፍ ለአቅርቦታቸው እና ለድሰታቸው እግዚአብሔርን እንደ ሕይወት የሚሹ ሰዎች ምንጭ ነው፤ የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ እስከ ሞት እና የዘላለም ጥፋት ድረስ እንደ መርዛቸው ሰይጣንን የተከተሉ ሰዎች ምንጭ ነው—ዮሐ. 1፡4፤ 15፡1፤ 8፡44።

ሐ. የመጀመሪያው መንገድ በዘላለማዊ ሕይወቱ እንደ አቅርቦት ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲሹ፣ እግዚአብሔርን እንዲያተርፉ እና እግዚአብሔርን እንዲደሰቱ የሆነ የሕይወት መንገድ፣ ጠባቡ መንገድ ነው፤ ሁለተኛው መንገድ ሰዎች ልጆቹ ለመሆን ሰይጣንን እንዲከተሉ የሆነ የሞት እና የመልካምና የክፉ መንገድ፣ ሰፊው መንገድ ነው—ማቴ. 7፡13-14፤ ሐዋ. 9፡2፤ 1 ዮሐ. 3፡10።

መ. የመጀመሪያው መርህ የሕይወት መርህ—በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ የመሆን መርህ—ነው፤ ሁለተኛው መርህ የሞት እና የመልካምና የክፉ መርህ—ከእግዚአብሔር ኢ-ጥገኛ የመሆን መርህ—ነው—ዘፍ. 4፡3-4፤ ኤር. 17፡5-8፤ ዮሐ. 15፡5።

ሠ. ሁለቱ መጠናቀቆች የሁለቱ ዛፎች፣ የሁለቱ ምንጮች፣ የሁለቱ መንገዶች እና የሁለቱ መርሆች የመጨረሻ ውጤት ናቸው፡-

1. የእግዚአብሔር የሕይወት መንገድ መጠናቀቅ የሕይወት ውኃ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት—ራእ. 21፡2፣ 9-11፤ 22፡1-2።
2. የሞት እና የመልካምና የክፉ መንገድ መጠናቀቅ የእሳት ባሕር ነው—19፡20፤ 20፡10፣ 14-15።

**II. የእግዚአብሔር ውጥን በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር ያለ ኢዮብ ሳይሆን በሕይወት ዛፍ መስመር ያለ ኢዮብ እንዲኖረው ነበር፡-**

ሀ. የኢዮብ እና የባልንጀሮቹ አመክንዮ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር መሠረት ነበር፤ ያለ መለኮታዊው መገለጥ እና ያለ መለኮታዊው ሕይወት ልምምድ ነበሩ—ኢዮብ 2፡11—32፡1።

ለ. ኢዮብ፣ እንደ ባልንጀሮቹ፣ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ባለማወቅ በትክክል እና በስህተት እውቀት ቆሞ ነበር—4፡7-8፡-

1. ኢዮብ ወይም ባልንጀሮቹ ሰው እንዲሆን እግዚአብሔር በወሰነው በሕይወት ዛፍ መስመር ውስጥ አልነበሩም—ዘፍ. 2፡9።
2. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የነበራቸው ጽንሰ-ሃሳብ የተገነባው በመልካም እና በክፉ፣ በትክክል እና በስህተት፣ ፈጽሞ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መርህ መሠረት እና ፈጽሞ በሰው፣ በወደቀው ሰው የሥነ-ምግባር ጽንሰ-ሃሳብ መሠረት ላይ ነበር—ኢዮብ 8፡1-20።

ሐ. ኢዮብ እና ባልንጀሮቹ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ ክልል ውስጥ ነበሩ፤ እግዚአብሔር ከዚያ ክልል ሊያድናቸው እና በሕይወት ዛፍ ክልል ውስጥ ሊያስቀምጣቸው እየሞከረ ነበር—1፡1፤ 2፡3፤ 19፡10።

መ. ኢዮብን በማስተካከሉ ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር አላማ ከመልካም እና ከክፉ መንገድ ወደ ሕይወት መንገድ እርሱን ለማዞር ነበር ይኸውም እግዚአብሔርን በሙላት ማትረፍ ይችል ዘንድ ነው—42፡1-6።

**III. የሕይወት ዛፍ ራእይ ያስፈልገናል—ዘፍ. 2፡9፤ ራእ. 22፡1-2፣ 14፡-**

ሀ. የሕይወት ዛፍ የሚያመለክተው ሦስታንዱ አምላክ በክርስቶስ ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ እንደ ሕይወት በምግብ መልክ ራሱን ማደሉን ነው—ዘፍ. 2፡9።

ለ. የሕይወት ዛፍ የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ነው፡-

1. በእግዚአብሔር አላማ መሠረት፣ ምድር የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ናት፣ ዔድን ገነት የምድር ማዕከል ናት፣ የሕይወት ዛፍ የዔድን ገነት ማዕከል ነው፤ ስለዚህ፣ አጽናፍ-ዓለም ማዕከሉን ያደረገው በሕይወት ዛፍ ላይ ነው።
2. ለእግዚአብሔርም ለሰውም ከሕይወት ዛፍ ይልቅ ማዕከላዊ እና ወሳኝ የሆነ ምንም ነገር የለም—3፡22፤ ራእ. 22፡14።

ሐ. አዲስ ኪዳን ክርስቶስ የሕይወት ዛፍ ስዕል ፍጻሜ እንደሆነ ይገልጣል—ዮሐ. 1፡4፤ 15፡5።

መ. በዮሐንስ ወንጌል የተገለጡት ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ገጽታዎች በሙሉ የሕይወት ዛፍ ውጤት ናቸው—6፡48፤ 8፡12፤ 10፡11፤ 11፡25፤ 14፡6።

ሠ. የሕይወት ዛፍ ድስታ በእግዚአብሔር የተዋጁ ሁሉ ዘላለማዊ እድል-ፈንታ ይሆናል—ራእ. 22፡1-2፣ 14፡-

1. የሕይወት ዛፍ እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ለሰው የወጠነውን ነገር ለዘላለም ይፈጽማል—ዘፍ. 1፡26፤ 2፡9።
2. የሕይወት ዛፍ ፍሬዎች በዘላለም ውስጥ በእግዚአብሔር ለተዋጁት ምግብ ይሆናል፤ እነዚህ ፍሬዎች በየወሩ በመፍራታቸው ያለማቋረጥ ትኩስ ይሆናሉ—ራእ. 22፡2።

## IV. በዘፍጥረት 2፡9 ያሉት ሁለት ዛፎች—የሕይወት ዛፍ እና የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ—ሁለት የመኖር መርሆችን ይወክላሉ፡-

ሀ. ሁለቱ ዛፎች አንድ ክርስቲያን በሁለት መርሆች—በትክክል እና በስህተት መርህ ወይም በሕይወት መርህ—መሠረት ሊኖር እንደሚችል ያሳያሉ—1 ቆሮ. 8፡1።

ለ. ኢዮብ እና ባልንጀሮቹ በሥነ-ምግባር ክልል የሆነ ነገርን ተከታተሉ፣ ነገር ግን እኛ፣ በክርስቶስ ውስጥ የሆንን አማኞች፣ በእግዚአብሔር ክልል የሆነ ነገርን መከታተል አለብን—15፡28፤ ኤፌ. 3፡16-21።

ሐ. ክርስቲያን መሆን በትክክል እና በስህተት መርህ፣ በመልካም እና በክፉ መርህ የመሆን ጉዳይ ሳይሆን የሕይወት ጉዳይ ነው—1 ዮሐ. 5፡11-13፣ 20፡-

1. ጌታ ኢየሱስን በተቀበልን እና አዲስ ሕይወት ባገኘን ጊዜ፣ ሌላ የመኖር መርህ—የሕይወት መርህ—አገኘን፤ ይህን መርህ ካላወቅነው፣ የሕይወትን መርህ ወደ ጎን እናደርግና የትክክል እና የስህተት መርህን እንከተላለን።
2. በተግባራዊ ሕይወታችን በሕይወት ዛፍ መስመር ሳይሆን በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር ልንሆን እንችላለን—ምሳ. 16፡25፤ 21፡2።
3. በየዕለት ሕይወታችን በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መርህ ክልል ውስጥ ሳይሆን ሕይወት-በሚሰጠው መንፈስ ክልል ውስጥ መሆን አለብን—1 ቆሮ. 15፡45፤ ሮሜ 8፡2።
4. በሕይወት ዛፍ መርህ መሠረት ለመኖር፣ የውስጡን የሕይወት ስሜት መከተል ያስፈልገናል—ቁ. 6፤ ኤፌ. 4፡18-19፤ ኢሳ. 40፡31፡-
   ሀ. የሕይወት ስሜት በአሉታዊ ጎኑ የሞት ስሜት ነው—ሮሜ 8፡6።
   ለ. የሕይወት ስሜት በአዎንታዊ ጎኑ ከጥንካሬ፣ ከእርካታ፣ ከእረፍት፣ ከብሩህነት እና ከምቾት ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ጋር የሕይወት እና የሰላም ስሜት ነው—ቁ. 6።
5. በሕይወት ዛፍ መርህ መሠረት ስንኖር፣ ግድ የምንሰኘው ለመልካም እና ለክፉ ሳይሆን ለሕይወት ይሆናል፣ ነገሮችንም የምንለየው በትክክል እና በስህተት መርህ መሠረት ሳይሆን በሕይወት እና በሞት መሠረት ይሆናል—ዘፍ. 2፡9፣ 16-17፤ 2 ቆሮ. 11፡3።

## V. እያንዳንዱ በክርስቶስ ውስጥ የሆነ እውነተኛ አማኝ በመንፈሱ እግዚአብሔር እንደ የሕይወት ዛፍ በሥጋው ደግሞ ሰይጣን እንደ የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ ያለው ትንሹ የዔድን ገነት ነው—ዘፍ. 2፡9፤ ሮሜ 8፡2፣ 5-6፡-

ሀ. እግዚአብሔርን፣ ሰውን እና ሰይጣንን የሚያሳትፈው ሦስት-ማዕዘናዊ ሁኔታ በውስጣችን አሁን ስለሆነ ትንንሽ የዔድን ገነት ነን—ዘፍ. 1፡27-29፤ 2፡9፣ 16-17፡-

1. ሰው ከመውደቁ በፊት፣ የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ እና የሕይወት ዛፍ ከሰው ውጪ ነበሩ—ቁ. 9፣ 16-17።
2. በውድቀት በኩል የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ ውስጣችን ነው፣ ዳግም በመወለድ በኩል ደግሞ የሕይወት ዛፍ አሁን ውስጣችን ነው።
3. መንፈሳችን ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ተዋሕዷል፣ ሥጋ የሆነው አካላችን ደግሞ ከሰይጣን ኃጢአተኛ ንጥረ-ነገር ጋር ተደባልቋል (1 ቆሮ. 6፡17፤ ሮሜ 5፡12፤ 6፡6፣ 12)፤ ይህ ክርስቲያንን ትንሿ የዔድን ገነት ያደርገዋል።

ለ. በዘፍጥረት 2 በአዳም እንደተወከሉ ሰዎች፣ በመንፈሳችን የሕይወት ዛፍ በሥጋችን ደግሞ የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ አለን—ቁ. 9፤ ራእ. 2፡7፤ 22፡14፡-

1. የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍን በነካን ጊዜ ሁሉ ሙት እንሆናለን፤ የሕይወትን ዘፍ በነካን ጊዜ ሁሉ ሕይወት እናገኛለን—ሮሜ 8፡5-6፣ 10።
2. በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ ጎን ከቆምን እና ሰይጣንን ከነካን፣ የሰይጣንን፣ የዲያቢሎስን ሕይወት እንኖራለን፣ ውጤቱም ሞት ይሆናል—2 ቆሮ. 11፡3፤ ሮሜ 3፡23፤ 1 ዮሐ. 3፡4።
3. በሕይወት ዛፍ ጎን ከቆምን እና እግዚአብሔርን ከነካን፣ እግዚአብሔርን እንኖራለን፣ ውጤቱም ሕይወት ይሆናል—ዮሐ. 11፡25፤ 14፡6፤ 15፡1፣ 4-5።

ሐ. ሮሜ 8፡5-6 በአንድ ጎን *ሥጋ* እና ሞት፣ በሌላ ጎን መንፈስ እና ሕይወት፣ በመካከል ደግሞ አእምሮ ያለውን ትንሿን የዔድን ገነት ያሳያል፡-

1. ማንነታችንን በመንፈሳችን ወደሚያድረው ወደ ሕያዉ ማንነት ማዞር እና ከእርሱ ጋር አንድ ሆነን መቆየት እንደሚያስፈልገን ከሮሜ 8 እንማራለን—ቁ. 6፤ 1 ቆሮ. 6፡17።
2. አእምሮአችንን በመንፈስ ላይ ስናደርግ፣ ሕይወት፣ ሰላም፣ ብርሃን፣ ምቾት እና ጥንካሬ አለን፤ ጥማችን ይቆረጣል ረሀባችንም ይረካል—ሮሜ 8፡5፣ 6፤ ዮሐ. 4፡14፤ 7፡37-38፤ ማቴ. 5፡6።
3. አእምሮአችንን በመንፈስ ላይ ስናደርግ፣ አእምሮአችን በሕይወት እና በሰላም የተሞላ ነው—ሮሜ 8፡6፡-
   ሀ. ሰላም ያለን በውጫዊ ጠባያችን እና በውስጡ ማንነታችን መካከል አለመስማማት ስለሌለ ነው—ቁ. 6፤ ኢሳ. 9፡6-7፤ 26፡3።
   ለ. አእምሮአችን በመንፈስ ላይ ሆኖ በምንናገር ጊዜ፣ ከጌታ ጋር አንድ መንፈስ ስለሆንን በቃሎቻችን ውስጥ ሕይወት አካል ለብሷል—ምሳ. 18፡21፤ ዮሐ. 6፡63፤ ኤፌ. 4፡29።

*© 2020 Living Stream Ministry*